ክርስቲያናዊ በዓላትና

ታቦት

በኢትዮጲያ

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸውን?

ክርስቲያናዊ ይዘት አላቸው?

ይህ ጽሁፍ በበቂ መረጃ የተደገፈ ስለሆነ ከታሪክና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በንጽጽር በማየት ሰዎች እውነታውን እንዲያውቁ ያበረታታል።

የጽሁፉ አላማ የህዝበ ክርስትና እምነት ተቋማትን ለመቃወም ወይም የአንዱ አምልኮ ከሌላው ይሻላል በሚል ሁከት ለማስነሳት ሳይሆን ሰዎች ለምንና እንዴት በማለት በነጻነት ተነሳስተው ሃቁን እንዲመረምሩ ይጋብዛል። ላለፉት አስራ ዘጠኝ መቶ ዓመታት የክርስትና እምነት ከሰላሳ ሺህ በላይ በሚበልጡ ትላልቅና አናሳ በሆኑ ድርጅቶች ተከፋፍላለች። እንዲሁም በክርስትና ሥም በተደጋጋሚ በተደረጉ የመስቀል ጦርነቶች ቁጥር ስፍር የሌላቸው ሰዎች ሞተዋል። በ1ኛውና በ2ኛው ዓለም ጦርነት የክርስትና ተቋማት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በጦርነት በመሳተፍ የሚሊዮኖች ሕይወት እንዲቀጠፍ አስተዋጽኦ በማድረግ እጇ ቻቸው በደም ተጨማልቋል። ስለዚህ ክርስትናን ከክርስቲያን ነን ባዮችን ለይቶ ማወቅ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ምክኒያቱም የሰዎች የመዳን ዋስትና የተረጋገጠው እውነትን በማወቅ ላይ የተመሰረተ ነው።

ስለዚህ ጽሁፉ ከማውጫው ግርጌ በምእራፍና በርዕስ ተከፋፍሎ ስለተቀመጠ ከታች ርዕሱን በመጫን ያነቡ ዘንድ ለአንባብያን ቀለል ተድርጎ ቀርቧል።ጹሁፉ እንዳይንዛዛና ብዙዎችን እንዳያደናግር የመጽሐፍ ቅዱስ የመረጃ ጥቅሶች የተቀመጡት በዓላት ለምንና እንዴት በሚለው ላይ ነው።

መልካም ንባብ ይሁንልዎ!

ከአቶ ቱፋ ዘለቀ ሃጎስ

የማውጫ ርዕሳት

1. የኢትዮጲያ አዲስ ዓመት (እንቁጣጣሽ)
2. የደመራ (መስቀል) በዓል
3. የኢሬቻ በዓል ክርስቲያናዊ ነው?
4. የአሸንዳ፣ሶለል ወይም እንጊቻ
5. የጥምቀት በዓል (ከተራ)
6. ህዝበ-ክርስትናና የታቦት አምልኮ ሥርዓት
7. ከወር መጀመሪያ እስከ ወር መባቻ የሚዘከሩ በዓላት
8. የቡሄ (መላጣ ገላጣ) በዓል
9. የፋሲካ ትንሳኤ (ኢስተር ፣ኢሽታር)
10. ገና (ልደት)

የኢትዮጲያ አዲስ ዓመት (እንቁጣጣሽ)

የበዓላት አመጣጥ በአምልኮህ ላይ ለውጥ ያመጣል?

መልሱ አዎ! ያመጣል። ከእውነተኛው አምልኮ ጎን መቆም እንድንችል “ርኩስ ነገር አትንኩ” ሲል እውነተኛ አምላኪዎችን ያሳሰበውን የነቢዩ ኢሳይያስን አመለካከት መጋራት አለብን። — ኢሳይያስ 52:11

ይህ በየዓመቱ መስከረም አንድ ቀን በኢትዮጲያ የሚከበረው የአዲስ ዓመት መግቢያ ከአምልኮና ከሃይማኖት ጋር ትስስር አለው። ስለዚህ ታሪካዊ አመጣጡትን ማወቅ ተገቢ ነው። የዘመን አቆጣጠር ወይም የቀመሩ ባለቤት ከሆነችው ግብጽ መነሳት የግድ ይላል። ምክኒያቱም ባለቤትነቱን የተዋህዶ ኦርቶዶክስ በፍትሃ ነገስት ላይ በይፋ አስቀምጣለች።

ስለዚህ የተዋህዶ ኦርቶዶክስ አናት የሆነችው የኮፕት ኦርቶዶክስ እንቁጣጣሽን ወይም የዓመቱን መጀመሪያ በተመለከተ የአዲስ ዓመት ክብረ-በዓል ወይም የዘመን መለወጫ የሚከበርበት ቀን ቱት/Thout 1 መስከረም አንድ 11/ሴፕተምበር የኮፕት ቤተክርስቲያን ድረገጽ እንዲህ በማለት ይጀምራል:-

የግብጽ ቤተክርስቲያን የኮፕት አዲስ ዓመትን [ኢድ-ኣል ናይሩዝ Eid EL Nayrouz] የምታከብረው የሰማእት ዓመት (Anno Martyrs) ሲሆን የጥንቱን የግብጽ የወንድና የሴት አማልክትን በማሰብ የእርሻ የዘርና የመኸር ሶስቱን ወቅቶች (የናየል/አባይ) የእርሻ ኡደት ለመዘከር ነው። በመቀጠልም በ249 ዓ.ም በሮም መንግሥት ለተገደሉትና ለተሰቃዩት የግብጽ ክርስቲያኖች ነው ሲል ያትታል.....።

http://st-takla.org/Feastes-&-Special-Events/Nayrouz-Coptic-New-Year-Eid-El-Nairouz/Coptic-Year-Eid-Al-Nayroz-or-Nairoz-or-Nairuz_02-Happy-Coptic-New-Year-1724.html

ታሪካዊ አመጣጡ ይህ ከሆነ ከክርስትና በፊት ለሺህ ዓመታት ሲከበር የኖረ የአረማውያን የዘመን መለወጫ በዓል፡በፍጥነት የክርስትና ካባ ደርቦ ለሺህ ዓመታት ሲከበር ከኖረ ታሪክንና እውነት በሚሹ ሰዎች አእምሮ ውስጥ ብዙ ጥያቄ ያስነሳል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ

ድጋፍ የለውም። ነገር ግን ክርስቲያናዊ ይዘት እንዲኖረው በመደረጉ ለብዙዎች የክርስቲያን በዓል መስሎ ሊታያቸው ይችላል።እውነታው ግን ከዚህ የራቀ ነው።በዓላት የክርስትና ካባ የደረቡ ስለሆነ ክርስትናን ከክርስቲያን-ነን ባዮች ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ነው!

ስለ ሰማዕት ዝካሬ በተመለከተ ምንጩ የአረማዊ እምነት እንደሆነ ፡ ህዝበ ክርስትናም ይህንን እምነት ከየት እንደወሰደች ኢንሳይክሎፔድያ ብሪታኒካ እንዲህ ይላል:- “የነፍሳት ሁሉ ቀን . . . ወደ ሰማይ የሄዱትን ታማኝ ሰዎች ለማስታወስ በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የተወሰነ ቀን ነው። የበዓሉ አከባበር የተመሠረተው ታማኝ ሰዎች ሲሞቱ ነፍሶቻቸው ከቀላል ኃጢአቶች ካልነጹ ወይም ላለፈው ኃጢአታቸው ይቅርታና ዕርቅ ካላገኙ ወደ ብፅዓት ቦታ ሊገቡ አይችሉም። ወደዚህ የብፅዓት ቦታ ለመግባት እንዲችሉ በጸሎትና በሥርዓተ ቅዳሴ ላይ በሚቀርበው መሥዋዕት መርዳት ይቻል ይሆናል በሚለው ትምህርት ላይ ነው። . . . ከነፍሳት ሁሉ ቀን ጋር ዝምድና ያላቸው አንዳንድ በሕዝብ ዘንድ የታወቁ እምነቶች ምንጫቸው አረማዊና በጣም ጥንታዊ ነው። የካቶሊክ እምነት በተስፋፋባቸው በብዙ አገሮች የሚኖሩ የገጠር ሰዎች የነፍሳት ሁሉ ቀን በሚከበርበት ምሽት ሙታን ድሮ ይኖሩ ወደነበሩበት ቤት ተመልሰው በመምጣት በሕይወት ያሉት ከሚበሉት ምግብ ይካፈላሉ ብለው ያምናሉ።”

ከላይ የግብጽ ኮፕት ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እንደዘገበው በዓሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ የሌለውና የአህዛብ አማልክትን ለመዘከር ክርስቲያናዊ ጭምብል የለበሰ ወግ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጲያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ከግብጽ የወረሰችውን የዘመን መለወጫ ቀን በይፋ በፍትሃ ነገሥት ላይ መቼና እንዴት እንደተጀመረ ለታሪክ አስቀምጣለች። ድንጋጌውም በሀገሪቱ ሥርወ-ህግ ሆኖ ብዙ ዘመን የተሰራበት ከመሆኑ ጋር አሁንም የህግ ምንጭነቱን እንደያዘ ነው። ይህ መጽሐፍ ከአረብኛ ወደ ግዕዝ ተተርጉሞ በሥራ ላይ የዋለው[1444-1468 በአጼ ዘርዐያቆብ] የንግስና ዘመን ነው።(ገጽ አንድ መግለጫ fteha/04) በዓሉ መከበር ከጀመረ ስድስት ዘመናትን ላለማስቆጠሩ ፍተሃ-ነገሥት በቂ መረጃ ሰጥቶናል።

http://cdn.good-amharic-books.com/fiteha-1-cr.pdf

ኢትዮጲያ የግብጽን አዲስ ዓመት እንዴት ወረሰች?

በ325 ዓ.ም የኒቂያው ድንጋጌ #42 የግብጽ እስክንድርያው በዓለመንበረ ሥልጣን በኢትዮጲያ ላይ የበላይነት ስላለው በክርስትና ሥም የሚመጡ ድንበር ዘለል ወነችን ህዝቡ እንዲወርስ ህዝበ ክርስትና አስተዋጽዖ አድርጋለች አንቀጽ 4 ቁጥር 50 ገጽ 30

እንዲያውም በይፋ ከግብጽ በስተደቡብ ላሉት ሌሎቹ ብሄራት ወይም መንግሥታት የራሳቸውን ጳጳስ እንዳይሾሙ ኮፐት ትሹምላቸው ይላል። ሌሎቹ ሲል ጥቁሮቹ ጳያይሞቹ እንዳይሉ ፈርተው ነው? ከታች ያለውን የድረገጽ አገናኝ ጣቢያ ይጫኑ አለያም ገጹንና ቁጥሩን በመለጥ ያንብቡ።

http://cdn.good-amharic-books.com/fiteha-2-cr.pdf

እስካሁን እንደተመለከትነው የዘመን መለወጫ በዓል አከባበር ከአረማዊ ልማዶች ጋር የተሳሰረ ነው። የሐሰት አምልኮ በአምላክ ዓይን ርኩስና አስጸያፊ በመሆኑ ክርስቲያኖች የዚህ ዓይነት መሠረት ካላቸው ልማዶች ይርቃሉ። (ዘዳግም 18:9-12፤ ሕዝቅኤል 22:3, 4) ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል:- “ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው?” ጳውሎስ “ርኵስንም አትንኩ” በማለት ጨምሮ የተናገረበት በቂ ምክንያት ነበረው። — 2 ቆሮንቶስ 6:14-17

የዛር ፣ የጥንቆላ ፣ የመተትና የእርኩስ መንፈሥ ተግባራት የዘመን መለወጫ በዓላት መገለጫ መሆናቸው ሊካድ የማይቻል ሃቅ ነው። በዕንቁጣጣሽ ዋዜማ ምሽት የሚካሄዱ ክንውኖችን አስታውስ!

ክርስትያኖች በአጉል እምነቶች መካፈል ደስታንም ሆነ ብልጽግናን ለማግኘት ዋስትና እንደማይሆንና ከሁሉ በላይ ደግሞ የእውነተኛውን አምላክ ሞገስም እንደሚያሳጣ ይገነዘባሉ። (መክብብ 9:11፤ ኢሳይያስ 65:11, 12) በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች በአኗኗራቸው ልከኞችና ራሳቸውን የሚገዙ እንዲሆኑ አጥብቆ ይመክራል። (1 ጢሞቴዎስ 3:2, 11) በግልጽ ለመረዳት እንደሚቻለው የክርስቶስን ትምህርቶች እንደሚከተል ለሚናገር ሰው በእንደዚህ ዓይነት መረን የለቀቀ የፈንጠዝያ በዓል መካፈል ተገቢ አይሆንም።

የአዲስ አመት መልካም ምኞት መግለጫ በሚደረገው የስጦታ ልውውጥ ምንግዜም አምላክ ይህንን ያድርግልህ! ያድርግልሽ! የሚል አባባል መጠቀሱ አይቀሬ ነው። ሆኖም ምኞት፣ መሻትና ምስጋና ለእውነተኛው አምላክ እንደማይሆን ግልጽ ነው። ምክኒያቱም ይህ በዓል

በግልጽ የሚከበረው የግብጽ አማልክት በሚዘከሩበት ቀን ስለሆነ ከንጹህ አምልኮ ጋር ምንም ግኑኝነት የለው። የዘመን መለወጫው በሚከበርበት ዕለት በቤተክርስትያን ቡራኬና በቀሳውስት ዝማሬ እንዲሁም በመረዋ ደወል ቀኑ ተጀምሮ መረን በለቀቀ ስካር ይደመደማል።

መስቀል የጥንት የግብጽ አማልክት
መለያ ምልክት ነው።
ሃፒ ደግም ከወንዞች አማልክት አንዱ ነው።

የደመራ (መስቀል) በዓል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ?

ነገሮች ሁሉ መነሻ አላቸው። በየአመቱ በመስቀል በዓለ ዋዜማ በሚደረገው የደመራ እሳት ከመከናወኑ በፊት ከሃያ ደቂቃ ባልበለጠ የቀሳውስት ንግግር ላይ ሁልግዜም የሚጠቀስ አንድ ታሪክ አለ። ይኸውም የቆንስጣንጢና የእሌኒ ታሪክ ነው። ይህ ንጉሥ በህዝበ ክርስትና ቀሳውስት ቅዱስ በመባል ይታወቃል። ሆኖም ንጉሥ ቆንስጣንጢን ዓለማዊው ፈላጭ ቆራጭ ንጉሥ ሲሆን በምእራባውያን ክፉ መናፍስት የተጠናወተው መሪ በመባልም ይታወቃል። በእርሱም ዘመን ክርስትና ለሁለት እንድትከፈልና ብሄራዊ ሃይማኖት እንድትሆን ሲደነግግ መስቀል ደግሞ የሃይማኖቱ መለያ አርማ እንዲሆን አድርጓል። የርሱን ትዕዛዝ ያልተቀበሉትን የክርስቲያን የበላይ አካላት በግፍ እንዲታሰሩ ያደረገ መሪ ነበር። ቆንስጣንጢን ሲታወስ አረማዊ የጣኦት ምልክት መስቀል ያታወሳል። የቆንስጣንጢን ዓላማ ምንም ይሁን ምን መስቀል ከኢየሱስ ክርስቶስ እንዲሁም ከክርስትና እምነት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። እንዲያውም መስቀል ከአረማውያን የጣኦት የምስል አምልኮ ሥርዓት የተወረሰ የሃሰት ልማድ ነው።

http://www.sacred-texts.com/cla/pcc/pcc13.htm
http://dominicanewsonline.com/news/homepage/features/commentary/use-of-the-cross-in-worship-is-it-really-proper/

አለማዊው ንጉስ ቆንስጣንጢና የእሌኒን የመስቀል ታሪክ ወደ ጎን በመተው ይህ በዓል ኢትዮጲያ ውስጥ መከበር የተጀመረው መቼና እንዴት የሚለውን ጥያቄ መመለሱ ተገቢ ነው። እንዴት ተጀመረ ለሚለው በተለምዶ ህዝበ-ክርስትና የምትሰጠው ምክንያት አለ። እሱም ንጉስ ላሊበላ በመስቀል ጦርነት ወቅት ተዋግቶ ግማደ መስቀሉን አምጥቷል በማለት ታሪኩን ከንግሥት እሌኒ ጋር በማቆራኘት በደመራው ሥርዓተ ክንዋኔ ላይ በየአመቱ የሚተላለፈው አጭር መልዕክት ነው።

[ፍተሃነገሥት አንቀጽ 4 ቁጥር 50 ገጽ 30 ኒቅያ እዝ. 42] የግብጽ የኮፕት አብያተ ክርስትያን ለኢትዮጲያ እናት (የበላይ) ስለሆነ ማወቅ ነበረበት፣ሆኖም አያውቁትም። ነገር ግን የባዛንታይን ንጉስ ሄርክለስ በእንጨት ምክንያት ከፋርስ መንግሥት ጋር ጦርነት ማድረጉን የኮፕት ኦርቶዶክስ አምኗል። የኢየሱስ

ክርስቶስን እውነተኛ አስተምህሮት ችላ በማለት እልፍ አእላፍትን ለሞት ያደረገው ለአራት መቶ ዓመታት የዘለቀው የመስቀል ጦርነት የህዝበ-ክርስትናን ተቋማት እጅ በደም ተጠያቂ አያደርግምን? — ማቴዎስ 26፡52፣ 28፡19፣20

http://www.copt.org/2010/09/28/the-feast-of-the-cross/

ፍተሃ-ነገሥት የኦርቶዶክስ {ሸሪዓ} የህግና ሥርዓት መተዳደሪያ ስለሆነ በ14ኛው ክፍለ ዘመን በሥራ ላይ መዋሉን የመጽሐፉ መግቢያ ላይ ይገልጻል ሆኖም ስለ ደመራ በዓል ፍንጭ አይሰጥም። ንጉስ ላሊበላ በ13ኛው ክፍለ ዘመን የመስቀሉን ገድል ከሰሩ በ14ኛው ክፍለ ዘመን በሥራ ላይ የዋለው ፍተሃነገሥት ሌሎቹን የክርስትያን በዓላት ሲያካትት ደመራን አልፎታል። ሆኖም በዙ ፍንጭ ባይሰጡም በአንዳንድ የኢትዮ-ኦርቶዶክስ ታሪክ ውስጥ ለይስሙላ ተካተዋል።

https://en.wikipedia.org/wiki/Gebre_Mesqel_Lalibela

http://cdn.good-amharic-books.com/orthohist-4-cr.pdf

በየሀገሩ ያሉ የህዝ-በክርስትና ተከታዮች የምስራቁም ሆነ የምዕራቡ ይህንን በዓል በተመሳሳይ ቀን አያከብሩም፣ሥርዓተ ክንዋኔውም የተለያዬ ነው።

ይህ ሰዎች በተቀጣጠለ እንጨት ዙሪያ ተሰባስበው የሚያከናዉኑት የአምልኮ ሥርዓት በመጀመሪያዎች ክርስቲያኖች ያልተደረገና በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ የሌለ ስለሆነ ክርስቲያዊ አይደለም።— ዳንኤል3፡18 ዘጸአት 20፡4

ይህ ጥንታዊ የአህዛብ የጣኦት ሥርዓተ አምልኮ መልኩን በመቀየር የክርስቲያን ካባ ሰለደርበና እንዲሁም ኢየሱስ ከተሰቀለበት እንጨት ጋር ታሪኩን ስለ አዛመዱት የመፅሃፍ ቅዱስ ዕውቀት የሌላቸው ሰዎች የክርስቲያን በዓል መስሎ ሊታያቸው ይችላል። ቁም ነገሩ ግን ኢየሱስ ለእኛ ሲል በእንጨት ላይ በመሰቀሉ አዳነን እንጅ የተሰቀለበት ግዑዝ እንጨት አይደለም። — 1ኛ ቆሮንጦስ 10:14 ዘፀዓት 20:4, 5

የደመራ በዓል ስርዓተ ክንዋኔ

1: - በእሳቱ ዙሪያ ሰዎች ከበው የሚያደርጉት ጭፈራ የጣኦት ዉዳሜ ነው!

2: - እሳቱ ተቃጥሎ ሲያልቅ መስቀሉ በወደቀበት አቅጣጫ ሰሜን ቸነፈር ደቡብ ጥጋብ ነው ብሎ መተንበይ ጥንቆላ ነው! “ሟርትም አታሟርቱም!” — ሚኪያሥ 3:6.11 5:12 ሐጌ 1:10, 12 ዘካርያስ 10:1

3: - በዕለቱ በየቤቱ የሚደረገው የዛር ዳንኪራ የእርኩስ መንፈስ በዓል! — ምሳሌ 22:5

http://rationalwiki.org/wiki/Pagan_survivals

http://en.wikipedia.org/wiki/Bonfire

https://www.circlesanctuary.org/…/solstice-fires-of-the-pag…

http://www.theurbancampfire.com/2011/11/pagan-ritual

http://www.faeriefaith.net/festival.list.html

አንዳንድ ሰዎች እንደመከራከሪያ የሚያቀርቡት " ኢየሱስ እንጨቱን ተሸክሞ ይከተለኝ " (ማርቆስ 8:34) ያለውን ቃል በመደጋገም ሲገልፁ ይደመጣሉ። ይህ ማለት ግዑዝ እንጨት ተሸክሞ የሄደ ሁሉ የኢየሱስ ተከታይ ነው ማለት አይደለም። ነገር ግን በዕምነቱ እስከ ሞት ድረስ መፅናትን የሚጠቁም መረጃ ነው። እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ ሞት ያቆብም በሰይፍ አንገቱን ተቀላ እንዲሁም የሌሎችን የመጀመሪያው ዘመን ክርስቲያኖችን ታሪክ ማየት በቂ ማስረጃ ነው። ከምስል ጋር የሚያገናኘው ታሪክ የለም። እንጨት ተገኘ ብለው በእሳት ዙርያ ተሰባሰብው ዳንኪራ?...ፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስላልሆነ መመርመር ጥሩ ነው። — የሃዋርያት ሥራ 17:2, 3

ስለ ታሙዝ እና ስለ መስቀል እንዲሁም በእሳት ዙሪያ የሚደረግ የጣኦት አምልኮ ለማወቅ የድረገጽ አገናኝ ጣቢያውን በመጫን ታሪካዊ መረጃ ማግኘት ይችላሉ

http://www.albatrus.org/…/religio…/pagan/origin_of_cross.htm

http://www.britannica.com/EBchecked/topic/582039/Tammuz

ይህን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተገለጸ በዓል የመጀመሪያው ዘመን ክርስቲያኖች አላከበሩትም። የመስቀሉን ግኝት በተመለከተ ብዙ ተከታታይ አፈታሪኮችና ፈጠራ

እንዳለው ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ ሲገልጽ፡- ታሪኩ ግራ የሚያጋባና የሮማው ንጉስ እናት ሄለና ከሌሎች ሄለኖች ጋር ተውኔትና ያለው ስለሆነ በመላው ህዝበ ክርስትና ተወዳጅነት እንዳገኘ ይናገራል።

መስቀል ከክርስትና በፊት የአረማዊ የአምልኮ ምልክት ነበር። በሮማው ንጉስ በኮንስታንቲን አማካኝንት መስቀል የክርስቲያን መለያ ምልክት እንደሆነና ሰዎችም በአምልኮና በመቃብር ቦታዎች የመስቀል ምልክትን መጠቀም እንደጀመሩ ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ በሰፊው ያትታል።

https://www.britannica.com/topic/cross-religious-symbol

https://www.britannica.com/biography/Saint-Helena

በዘመናችን ደግሞ ክርስቲያን ነን በሚሉት ብሄራት በምስራቅ አውሮፓም ሆነ በም እራብ አውሮፓ አይርላንድ ኬልት እንዲሁም ስምሃን በአፍሪካ በሰሜን አሜሪካና በደቡብ ምስራቅ እስያ የሚኖሩ ጣኦት አምላኪዎች በእሳት ዙሪያ በመሳባሰብ የአምልኮ ሥርዓት ማካሄድ የተለመደ ነው።

የኢሬቻ በዓል ክርስቲያናዊ ነው?

አይደለም! መጽሐፍ ቅዱስዊ ድጋፍም የለውም። የክበረ በዓሉ ታዳሚዎቹም ይህንን ያውቁታል። ነገር ግን የአምልኮው ተካፋዮች ባብዛኛኛው ክርስቲያን ነን ባዮች ስለሆኑ ታሪካዊ አመጣጡን ማወቁ ጥንቃቄ ማድረጉ ለሕይወት ዋስትና አለው።

ይህንን የአምልኮ ስርዓት በተመለከተ ገዳ (gadaa) የተሰኘ ድረገጽ ታሪካዊ አመጣጡን አጠር ባለ መልኩ እንደሚከተለው ይገልጸዋል ፡-

"ከ12,000 ዓመት በፊት የፀሐይና የሰማይ አምላክ, የኩሽ ፈርኦን አምላክ, ታላቅ ወንድ ልጁ ኦቴ, ትልቁ ልጅ እና አሲስ (አቴቴ ወይም አድባር) የተሰኘች ሴት ልጅ ነበሩት። ታላቅ ወንድሙም ታናሹን ገደለው።

ግድያው በተፈጸመበት በግብፅ በናይል ወንዝ ዳርቻ ላይ የሞተውን ወንድሟ ኦራን ለሞተው ወንድና ሴት ኦዳ, እና አሲስ (አቴቴ ወይም አድባር) አንድ ዛፍ (ኦዳ) ተክለው ነበር, እና የፀሐይ አምላክ የሆነው አባቷን በሴኔት እና ኦራ ቤተሰቦች መካከል ሰላም እንዲሰፍን ለመታሰቢያ ይሆን አንድ ዛፍ ተክለው ነበር። ከዚያም በኋላ ዝናብ መጣ! ከዚያም የሰላም ዛፍ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ሆነ። ኋላም ያ ለመታሰቢያ የተተከለው ዛፍ ከስምንት ሺህ ዓመታት በኋላ በድንጋይ ሃውልት ተተካ።

ለ-ኦራ ሀውልት የሚከበረው በዓል በየአመቱ በመስከረም ወር አባይ በኑቢያና በግብፅ ሲፈስ ይከበራል። በኢትዮጵያ፣በአክሱማዊ እና ቅድመ-አክሱማዊ ዘመን፣ ከሞት ለተነሳው የፀሐይ አምላክ ልጅ ኦራ መታሰቢያ በአሴስ (አቴቴ ወይም አድባር) በተተከለው ሀውልት ዙሪያ ታላቅ በዓል ይከናወናል! በሁለቱ ወንድማማቾች መካከል የተፈጠረውን ሰላም በዘላቂነት ይቀጥላል። ከዚያም መታሰቢያነቱ እንዲጸና የፀሐይና የሰማይ አምላክን ቼቦ በማብራትና በማመስገን ይዘከራል፣ሲል አፈታሪኩ ሀተታውን ይገልጻል።

http://www.gadaa.com/IrreechaaAbout.html

አክሱም የሚለው ቃል በታሪክ እንደሚታወቀው (አክሹም) የኩሽ ጌታ ወይም አምላክ እንዲሁም በአገው ሰርወ ቃል ዋግሹም (ዋቅሹም) ሲሆን ቀድሞ ከግብጽ አማልክት ጋር ግንኙነት ያላቸው የዋቅ አምልኮ ስርዓትን ያመለክታል። ለዚህም ንጉሥ ኢዛና በመረዊ (ሰሜን ሱዳን) የነበሩትን ነገስታት ድል ካድረገ በኋላ ራሱን የኩሽ ንጉሥ በማለት ሲሰይም ድል አጎናጽፎኛል ብሎ ያመነበትን የግሪክ የጦርነት አምላክ አሪስን (ares) ተቀብሏል።

ይህ ታሪክ ከ350 ዓ.ም የተበረዘው የክርስትና ሃይማኖት ቢስፋፋም፣በሰባተኛው ዓ.ም አዲስ በማቆጥቆጥ ላይ በነበረውን የእስላምና እምነት ላይ ተጽዕኖ ለማድርግ አልቻለም። ህዝቡ በሰሜንም ሆነ በደቡብ በክርስትና ስም የቀድሞውን የአምልኮ ስርዓት እንደቀጠለ ነበር።

ታዲያ ዛሬ በአክሱም ከተማ ላይ ቆመው የሚታዩት ሃውልቶች ለቀድሞ የሃሰት አማልክት መታሰቢያነት የተቀረጹ ናቸው። በእርግጥ በአካባቢው የህዝበ ክርስትና ቤተ ክርስትያን ቢኖርም ከክርስትና ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የላቸውም።

ኢንሳይክሎፒዲያ ዊኪፒዲያ የምስጋና ቀን ሲል የገልጸዋል ፣ በተለያዩ ድረገጾችም ተመሳሳይ ሃሳብና ትርጉም አላቸው። ሆኖም ችግሩ የባህል ወይም የማንነት መገለጫ ሳይሆን ከማንንት ባሻገር ያለው የአጉል እምነትና የሐሰት አምልኮ ሰላባ መሆኑ ነው። ኢሬቻ የምስጋና ቀን ከሆነ ምስጋናው ለማን ነው? የጥንት የግብጽ ፈረኦንና ነገሥታትን ማዳን ላልቻሉ የሃሰት አማልክትን ከሆነ ትልቅ ስህተት ነው።

https://en.wikipedia.org/wiki/Irreechaa

ከአጉል እምነትም ሆነ ከሐሰት ሃይማኖት በስተ ጀርባ አንድ የማይታይ አካል አለ። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ አካል ሲናገር “የእግዚአብሔር አምሳል የሆነውን የክርስቶስ፣ የክብሩን ወንጌል ብርሃን እንዳያዩ፣ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን ሰዎች ልቡና አሳውሮአል” ብሏል። (2 ቆሮንቶስ 4:4) “የዚህ ዓለም አምላክ” የተባለው ከሰይጣን ዲያብሎስ ሌላ ማንም ሊሆን አይችልም። ሰይጣን የሐሰት አምልኮን በማስፋፋት ረገድ ዋና ተዋናይ ነው። ጳውሎስ “ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክ ለመምሰል ራሱን ይለዋውጣል” ሲል ጽፏል። አክሎም “እንግዲህ የእርሱ አገልጋዮች፣ የጽድቅ አገልጋዮች ለመምሰል ራሳቸውን ቢለውጡ የሚያስገርም አይደለም” ብሏል። (2 ቆሮንቶስ 11:14, 15) ሰይጣን መጥፎ ነገሮች መልካም መስለው እንዲታዩ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ሰዎች ውሸቶቹን እንዲያምኑ በማድረግ ያታልላቸዋል።

ልበ ቅን የሆኑ በርካታ ሰዎች ስለ አምላክም ሆነ ስለ ሰው ዘር የወደፊት ሁኔታ ትክክለኛ እውቀት የላቸውም። በጥልቅ ለሚያሳስቧቸው መንፈሳዊ ጉዳዮች መልስ ማግኘት ባለመቻላቸው ግራ ተጋብተዋል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ፈጣሪያችንን በሚያሳዝኑ አጉል እምነቶች፣ የአምልኮ ሥርዓቶችና ክብረ በዓሎች ተጠላልፈዋል! የሐሰት ሃይማኖት ከመንግሥታት ጋር የመሠረተው ይህ ጥምረት በሰው ዘሮች ላይ ከፍተኛ ሥቃይ አስከትሏል። በሺዎች የሚቆጠሩት ሃይማኖቶች ተዋህደው አንድ ዓለም አቀፋዊ ድርጅት ባይመሠርቱም በዓላማና በድርጊት ተጣምረዋል።

ታዲያ አንተ ከዚህ ወጥመድ ለማምለጥ ምን ማድረግ ይገባሃል? አዎ ትችላለህ! እንዴት? የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሆነው የራእይ መጽሐፍ የሐሰት ሃይማኖትን እንዴት እንደሚገልጸው ተመልከት። የሐሰት ሃይማኖት በብዙ መንግሥታትና በሕዝቦቻቸው ላይ ተጽዕኖ በምታሳድር የሰከረች ጋለሞታ ተመስሏል። ይህቺ ምሳሌያዊት ሴት ከበርካታ ነገሥታት ጋር ከማመንዘሯም በላይ በአምላክ እውነተኛ አምላኪዎች ደም ሰክራለች። (ራእይ 17:1, 2, 6, 18) አስጸያፊና አስነዋሪ ከሆነው ድርጊቷ ጋር የሚስማማ "ታላቂቱ ባቢሎን፣ የአመንዝሮችና የምድር ርኩሰቶች እናት" የሚል ስም በግንባሯ ላይ ተጽፏል። —ራእይ 17:5

ስለዚህ "ከመካከላቸው ውጡ፤ ለእኔም የተለያችሁ ሁኑ፤ ይላል ጌታ። ርኩስ የሆነውን ነገር አትንኩ።" — 2 ቆሮንቶስ 6:17

ይህ የሐሰት አምልኮ የሚከበረው በኢትዮጲያ ብቻ ነው? ለማወቅ ከፈለግክ ሊንኮቹን በመጫን ተጨማሪ ሃሳብ ማግኘት ትችላለህ።

http://www.newadvent.org/cathen/13309a.htm

ለአማልክት የሳርና የቅቤ መስዋእት ማቅረብን በተመለከተ በጥንታዊቱ አውሮፖ ይደረግ እንደነበረና በህንድ ግን አሁንም የተቀደሰ ሳር ለአማልክት መስዋእት እንደሚያቀርቡ የኒው ካቶሊክ ኢንሳይክሎፒዲያ ይገልጻል።

በሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ አዝቴክስ ደግሞ የሳር የሴት አማልክት ደግሞ ቤተመቅደስ እንደነበራት ታሪክ ያስረዳል።

http://malinche.info/blog/?p=18

በኔፓል ተመሳሳይ የሳር መስዋእት

https://www.google.ca/url?sa=t&rct=j&q=&esrc=s&source=web&cd=2&cad=rja&uact=8&ved=0CCIQFjABahUKEwi_xsbB6anIAhWBND4KHVygA5g&url=http%3A%2F%2Ftasteofnepal.blogspot.com%2F2013%2F12%2Fdubo-grass-garland.html&usg=AFQjCNEgQjQJ8JCf5E0uE2PiRY8H507yFg

https://vedicgoddess.weebly.com/bhakti-masala-blog/durva-is-sacred-grassby-yogi-ananda-saraswathi

ሳርን በተመለከተ በማንኛውም የክርስትያን በዓላት ገና ፣ ፋሲካ ፣ አዲስ ዓመትና የመስቀል በዓላት ሁሉም በየቤቱ እርጥብ ሳር የመጎዝጎዝ ወግ የሃሰት አምልኮ አስተዋጽኦ ለመሆኑ አመላካች ነው።



የአሸንዳ፣ሶለል ወይም እንጊቻ በዓል ክርስቲያናዊ ነው?

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ ባይኖረውም የተዋህዶ ኦርቶዶክስ ሰለ ክብረ በዓሉ ተቃውሞ የላትም። ክርስቲያናዊ ካልሆነ የዚህ ክብረ በዓል ታሪካዊ አመጣጥን መመርመር አስፈላጊ ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ አሸንዳ ማለት ምን ማለት ነው። ይህ ቃል የተወሰደው በትግርኛም ሆነ በአካባቢው በሚነገሩ ቋንቋዎች ነው። በወንዝ ወይም በውሃ ዳርቻ ከሚበቅል ረጅም ቀጭን ሳር ነው። ሰንበሌጥ ወይም ፊላ ሳር ማለት ነው። በቁጥር አናሳ ከሆኑት የግዕዝ ቋንቋ ተናጋሪ ከሆኑት የመታህት (መታሂት) የተወሰደ ቃል ነው የሚለው አባባል ትክክለኛ ሊሆንም ላይሆንም ቢችልም፣ ስሜት የሚሰጥ መላ ምት ነው።

ስለዚህ ጉዳይ ዊኪፒዲያ ታሪካዊ ምንጩን ምናልባትም ከ400 ዓ.ም ሳይሆን አይቀርም ወይም እንደሚሉት ሲል በድረገጽ ላይ አስፍሯል። ያን ዋቢ በማድረግ ከቅድመ ክርስትና በፊት የነበሩትን አረማዊ በዓላትን በንጽጽር በማየት ወደ ታሪካዊው መነሻው ለመድረስ በቂ ፍንጭ ማግኘት እንችላለን።

https://en.wikipedia.org/wiki/Ashenda

በዓሉ በእብራይስጥም ሆነ በክርስቲያን ግሪክ ቅዱሳን መጻሕፍት በቂ መረጃ ከሌለው ምን ሊሆን ይችላል? ክርሲያናዊ እንዳይባል በ350 ዓ.ም በይፋ የሃገሪቱ ሃይማኖት እንዲሆን የተደነገገው እምነት የተበረዘ ክርስትና እንጅ እውነተኛው አልነበረም። ስለዚህ ከቅድመ ክርስትና በፊት የነበሩትን አረማዊ የአምልኮ ታሪክን መመርመር የግድ ይላል። ምክኒያቱም ይህ በልጃገረዶች ጭፈራና ፈንጠዚያ የሚከናወን የማወደስ ሥርዓት የሚያነጣጥረው አንድ ሴት ላይ ነው። እሷም ማርያም ወይም እመ-አምላክ ወይም የሴት አምላክ ላይ ነው።

በእርግጥ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ለሌላቸው ሰዎች የኢየሱስ እናት በሥም ስለተጠቀሰች በዓሉ ክርስቲያናዊ መስሎ ሊታያቸው ይችላል። ያም ቢሆን

ልጃገረዶች ከሺንጣቸው በታች በረጅም ሳር አሸብርቀው የተመልካችን ቀልብ በሚሲብ መልኩ በሚያደርጉት የወገብና የዳሌ እንቅስቃሴና ጭፈራ ከሴት አማልክት ጋር ምን ግንኙነት አለው?

በዓሉ የሚከበረው ከሁለት ሳምንት የፍልሰታ ጾም በኋላ ነው። ይህም በነሐሴ ወር አጋማሽ ላይ ሲሆን ከተዋህዶ ወግ ጋር ጥብቅ ትስስር እንዳለው ለመስመል የተደረግ ጥረት ቢሆንም ፍጹም ክርስቲያናው አይደለም። ምክኒያቱም የክርስትና ወግ በሀገሪቱ የመመሪያ ደንብ ሆኖ መቀጠል የጀመረው በ14ኛው ክፍለ ዘመን መሆኑን ፍትሃ-ነገሰትም ሆነ ሌሎች የተዋህዶ ታሪካዊ መጻህፍት ይገልጻሉ።

በበዓሉ ቀን ልጃገረዶች ተሰባስበው ባካባቢያቸው ወደሚገኘው ማርያም ቤተክርስትያን በመሄድ በማህበረ ቅዱሳን ዝማሬና ጭፈራ የውዳሴ ሥርዓት ያከናውናሉ። እመ አምላክ በማለት ይዘምራሉ።ለምን? አምላክ ስጋ ለባሽ እናት የለውም። ምክኒያቱም አዳምና ሄዋንን የፈጠረ አምላክ ነው። እሱ መንፈስ ነው መኖሪያውም በመንፈሳዊ ሰማያት ሰማያት ነው።— ኢሳያስ 6:1-5

በድጋሜ የፍልሰታ ጾም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባይሆንም በ325 ዓ.ም በኒቂያው ድንጋጌ ላይ ቢሰፍርም በኮፕት ኦርቶዶክስ የበላይነት የማሻሻያ ድንጋጌ ጸድቆ በኢትዮጲያ በስራ ላይ እንዲውል የተደረገው በ14ኛው ክፍለ ዘመን በአጼ ዘርዐያቆብ ሥርወ መንግሥት ነው። እንዲሁም አሸንዳ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የተላለፈ የአረማውያን የጣኦት አምልኮ ወግ እንጅ በጽሁፍ የተቀመጠ ታሪካዊ መረጃ የለውም። ገጽ አንድ መግለጫ fteha/04

http://cdn.good-amharic-books.com/fiteha-1-cr.pdf

እንደዚያ ከሆነ ከቅድመ ክርስትና በፊት የነበሩ የአረማውያን እምነት መለስ ብሎ መቃኘት አስፈላጊ ነው። ቁጥር ስፍር የሌላቸው የሴት አማልክት ቢኖሩም፣የሰማይ ንግሥትና የአምላክ እናት (እመ አምላክ) ስትሆን ባቢሎናውያን ኢሽታር (አስተረዮ) ግብጻውያኑ ደግሞ አሲስ (አቴቴ) በማለት ያመልኳታል። እሷም ከአንድ ሺህ በላይ የተለያዩ ስም ያላት በሁሉም ብሄራት የምትታወቅ የአማልክት እናት። ሴቶችም ወንዶችም ያመልኳታል። ምክኒያቱም የመዋለድና የመባዛት የሴት አማልክት ስለሆነች ወልደው ከብደውና በዝተው ተባዝተው በምድር ላይ እንዲኖሩ እሷ

ትባርከናለች የሚል እምነት አላቸው። ስለዚህ የቀድሞዋ የግብጽ አቴቴ የባቢሎኖዋ አስተረዮ በክርስትና ሥም ማርያም የሚል ጭምብል በመልበስ፣ በክርስትና ሥም በህዝበ ክርስትና ተቋማት እውቅና አግኝታ በየአመቱ ትዘከራለች።በየዓመቱ መስከረም 21 የምት ዘከረውን አስተረዮ ማርያምን መለስ ብለህ አስብ። ለምን አስተረዮ ልትባል ቻለች?

https://www.ancient-egypt-online.com/isis.html

ኢየሱስ ክርስቶስ ማርያም የአምላክ እናት እንደሆነች አንድም ቦታ አልተናገረም፤ የተለየ ክብር ሊሰጣት እንደሚገባም አልጠቀሰም። በአንድ ወቅት አንዲት ሴት፣ ማርያም የእሱ እናት የመሆን አስደሳች መብት በማግኘቷ ምክንያት ለየት ያለ ትኩረት ልትሰጣት ፈልጋ ነበር፤ ኢየሱስ ግን “ደስተኞችስ የአምላክን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው!” በማለት አርሟታል።— ሉቃስ 11:27, 28

“የአምላክ እናት” እንዲሁም “ቲኦቶኮስ” (ወላዲተ አምላክ) የሚሉት ሐረጎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኙም። ነገር ግን ‘የሰማይ ንግሥት’ ተብላ የተጠራችው ማርያም ሳትሆን ከሃዲ የሆኑ እስራኤላውያን ያመልኳት የነበረችው የሐሰት አምላክ ናት። (ኤርምያስ 44:15-19) ‘የሰማይ ንግሥት’ ተብላ የተጠራችው የባቢሎናውያን አምላክ የሆነችው ኢሽታር (አስታርቴ) ወይም አስተረዮ መሆኗ አያጠራጥርም።

ጥንት የነበሩ ክርስቲያኖች ማርያምን አላመለኩም፤ የተለየ ክብርም አልሰጧትም። አንድ የታሪክ ምሁር እንደገለጹት የጥንቶቹ ክርስቲያኖች “ኑፋቄዎችን ይቃወሙ የነበረ ከመሆኑም ሌላ ለማርያም ተገቢ ያልሆነ ትኩረት መስጠት ‘እንስት አምላክን ያመልካሉ የሚል ጥርጣሬ ያስነሳል’ የሚል ስጋት ሳይፈጥርባቸው አይቀርም።”— ኢን ኩዌስት ኦቭ ዘ ጂዊሽ ሜሪ

https://www.bc.edu/content/dam/bc1/schools/stm/continuing%20education/encore/pdf/In%20Quest%20of%20the%20Jewish%20Mary,%20022414.pdf

መጽሐፍ ቅዱስ አምላክ ምንጊዜም እንዳለ ይናገራል። (መዝሙር 90:1, 2፤ ኢሳይያስ 40:28) አምላክ መጀመሪያ ስለሌለው እናት ልትኖረው አትችልም። በተጨማሪም ማርያም አምላክን በማህፀኗ መያዝ አትችልም፤ ምክንያቱም አምላክን ሰማያት እንኳ ሊይዙት እንደማይችሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል።—1 ነገሥት 8:27

አንዳንዶች ማርያም የአምላክ እናት እንደሆነች የሚያምኑት ለምንድን ነው?

ለማርያም የተለየ ክብር መስጠት እንደተጀመረ የሚታሰበው ከአራተኛው መቶ ዘመን መገባደጃ አንስቶ ነው። በወቅቱ በሮም ግዛት ውስጥ የነበረው የመንግሥት ሃይማኖት የካቶሊክ እምነት ነበር። ይህም በርካታ አረማውያን ወደ ክርስትና እንዲለወጡ አደረጋቸው። በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያኗ ቅዱስ ጽሑፋዊ ድጋፍ የሌለውን የሥላሴ ትምህርት ተቀበለች።

የሥላሴ ትምህርት ደግሞ በርካታ የቤተ ክርስቲያኗ ተከታዮች ኢየሱስ አምላክ ከሆነ፣ ማርያም የአምላክ እናት መሆን አለባት ብለው እንዲደመድሙ አደረጋቸው። በ431 ዓ.ም በተደረገው የኤፌሶን ጉባኤ ላይ ቤተ ክርስቲያኗ ማርያም "የአምላክ እናት" ናት በማለት በይፋ አወጀች። ለማርያም አምልኮ አከል ክብር መስጠት የተጀመረውም ከኤፌሶኑ ጉባኤ በኋላ ነው። አረማዊ የነበሩት ሰዎች ቤተ ክርስቲያኗን ሲቀላቀሉ እንደ አርጤምስ (የሮማውያን ዲያና) እና አይሲስ የመሳሰሉት እንስት የመራባት አማልክቶቻቸው በድንግል ማርያም ሥዕሎችና ምስሎች ተተኩ።

በ432 ዓ.ም ፖፕ ሲክስተስ ሦስተኛ "ለአምላክ እናት" መታሰቢያ የሚሆን ቤተ ክርስቲያን እንዲገነባ ትእዛዝ አስተላለፉ። ቤተ ክርስቲያኑ የተገነባውም ሮማውያን ልጆች እንዲወለዱ ታደርጋለች ብለው ለሚያመልኳት ለሉሲና ክብር ተገንብቶ በነበረው ቤተ መቅደስ አቅራቢያ ነው። አንዲት ደራሲ ይህን ቤተ ክርስቲያን አስመልክተው ሲናገሩ "አረማውያን ለታላቋ እናት ያቀርቡት የነበረው አምልኮ፣ ሮም ክርስትናን ስትቀበል በማርያም አምልኮ እንደተተካ የሚያሳይ ትልቅ ምሳሌ ነው" ብለዋል።—ሜሪ—ዘ ኮምፕሌት ሪሶርስ

https://books.google.ca/books/about/Mary_The_Complete_Resource.html?id=-KGvAwAAQBAJ&redir_esc=y

በእርግጥ የዚህ አይነት የበዓል ሥርዓት በሌሎች ሃገራትና ብሔራት ይከበር ይሆን?

አዎ! በቅድመ ክርስትና ዘመንም ሆነ አሁን ባለንበት በ21ኛው ክፍለ ዘመን ይህ በዓል በአለማችን ዙሪያ በተለያዩ ብሄራት በእስያ፣በአውስትራሊያ፣በአፍሪካ፣ በሰሜንና በደቡብ አሜሪካ ይከበራል። ቋንቋቸው ይለያይ እንጅ ሁሉም የሚያወድሱት የጥንት አባቶቻቸውን አማልክት ነው።

http://www.newadvent.org/cathen/13309a.htm
http://malinche.info/blog/?p=18
https://www.google.ca/url?sa=t&rct=j&q=&esrc=s&source=web&cd=2&cad=rja&uact=8&ved=0CCIQFjABahUKEwi_xsbB6anIAhWBND4KHVygA5g&url=http%3A%2F%2Ftasteofnepal.blogspot.com%2F2013%2F12%2Fdubo-grass-garland.html&usg=AFQjCNEgQjQJ8JCf5E0uE2PiRY8H507yFg
https://vedicgoddess.weebly.com/bhakti-masala-blog/durva-is-sacred-grassby-yogi-ananda-saraswathi

በድጋሚ ሳርን በተመለከተ በማንኛውም የክርስትያን በዓላት ገና ፣ ፋሲካ ፣ አዲስ ዓመትና የመስቀል በዓላት ሁሉም በየቤቱ እርጥብ ሳር የመጎዝጎዝ ወግ የሃሰት አምልኮ አስተዋጽኦ ለመሆኑ አመላካች ነው።

https://waaqeffannaa.org/irreecha/invitation-to-oromo-national-thanksgiving-day/

የሳር መስዋእትና ውዳሴ አረማዊ አምልኮ

የጥምቀት በዓል (ከተራ) ክርስቲያናዊ ነው?

በማያሻማ አገላለጽ አይደለም! ፍጹም ክርስቲያናዊ አይደለም!
መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍም የለውም። ታዲያ ከየት መጣ?

የጥምቀት በዓል ታሪካዊ አመጣጥ ምን እንደነበር የኮፕት ኦርቶዶክስ እናት የሆነችው የግሪክ ኦርቶዶክስ ህጋዊ ድረ-ገጽ ታሪኩን ሲገልጽ! እንዲህ ይላል :-

በዓለ-ብርሃናት (Epiphany feast of lights) በጀንዋሪ ስድስት እንዲከበር የተደረገበት ያን ቀን ኢዮን (Aeon) የተባለ የአሌካሳንደሪያ ጠባቂ አማልክት የተወለደበት ቀን ስለሆነ ነው ፣ ኢየሱስም ከኢዮን አንዱ ነው ብለው ግኖስቲክስ(Gnostic) የጥንት የግሪክ አህዛበ እምነት ተከታዮች ያምኑ ነበር። በመቀጥል :- “ይህንን ቀን ክርስቲያኖች እንዲያከብሩት የተደረገበት ምክንያት የግኖስቲክስን በዓል ለማክሸፍ ነው” ትለናለች ህዝበ ክርስትና። ከወደቁ አይቀር መንከባለል አይነት ጨዋታ! እንግዲህ ይህ የአረማውያን የጣዖት አምልኮ የክርስትናን ካባ ደርቦ እንደመጣ እንረዳለን። – 2 ቆሮንቶስ 11:13-15

https://www.goarch.org/-/the-feast-of-epiphany-the-feast-of-lights

http://www.goarch.org/ourfaith/ourfaith8383

ስለዚህ ሰው ሰራሽ ወግ እንጅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ የሌለው የክህደት ሥራ በየትኛውም መመዘኛ ክርስቲያናዊ ነው ልንል አንችልም።የጥንቱን የአረማዊ የጣኦት እምነት መልኩን በመቀየር ክርስቲያናዊ ይዘት እንዲይዝ በማድረግ የአማኞችን ስሜትና ቀልብ በመሳብ ብዙ ተከታዮችን እናፈራለን የሚል ከንቱ እቅድ ዛሬ ህዝበ ክርስትና እልፍ አእላፍትን ከንጹህ የአምልኮ ጎዳና እንዳወጣ ታሪክ ይመሰክራል።

በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን እናት የሆነችው የግብጽ ኮፕት ኦርቶዶክስ የኒቂያውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ በዘመኑ የግብጽ ታዋቂ ከተማ ለሆነው የአሌክሳንደርያ ዋና አማልክት “ኢዮን” እንዲዘከር ሲባል

በክርስትን ስም የኢየሱስ ጥምቀት በሚል ሽፋን በኢትዮጲያ እንዲከበር በታሪካዊ ሰነድ በቂ መረጃ ስላለ እውነታውን አንብቦ ማወቅ የአንባቢው መብትና ግዴታ ነው።

እነሆ፡- ፍትሃ-ነገስት አንቀጽ 19 ቁጥር 726 ገፅ 183 ላይ እንዲህ ይላል ፡-" ክርስቶስ በዮሃንስ እጅ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ በግብፃውያኑ በአምስተኛው ወር በ11ኛው ቀን ነው ፤"ኤጲፋንያን" ጥምቀት ቅዳሴው በመንፈቀ ሌሊት ይሁን! (ይህ ማለት በኛ ታህሣሥ 11 መሆኑ ነው)። የምንጠቀመው የኮፐት የዘመን መቁጠሪያ ለመሆኑ ፍንጭ ሰጭ ነው።

ፍትሃ ነገስት ከአረበኛ ወደ ግዕዝ የተተረጎመውና በስራ ላይ የዋለው (1444ዓ.ም - 1468ዓ.ም) ባለው ጊዜ በአፄ ዘርዐያዕቆብ የሥልጣን ዘመን ነው። ይህ ጽሁፍ በሃገሪቱ ሥርወ-ህግ ሆኖ ብዙ ዘመን የተሰራበት በመሆኑ ፤ አሁንም ህግ ምንጭነቱን እንደያዘ ይገኛል።

http://cdn.good-amharic-books.com/fiteha-9-cr.pdf

በዓሉ በክርስትና ስም በግብጽ በምስራቅና በምእራብ አውሮፓ መከበር የጀመረው በሶስተኛው መቶ ዘመን አጋማሽ ገደማ (361 ዓ.ም) መሆኑን ይኸው ድረ-ገጽ ያትታል። በኢትዮጲያ ደግሞ በአስራ አራተኛው ክፍለ ዘመን እንደሆነ ፍተሃ ነገስት ይገልጻል።

ጥምቀትን በተመለከተ ኢየሱስ ምን አለ?

ማቴዎስ 28:19, 20 ፡- "ስለዚህ ሂዱና ከሁሉም ብሄራት ደቀ መዛሙርት አድርጉ ፤በአብ ፤በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁዋቸው ..... ከእናንተ ጋር ነኝ።" የኢየሱስ ትዕዛዝ ሂዱና የምስራቹን ቃል ስበኩ የአመኑትን አጥምቁ እንጅ በአመት አንድ ጊዜ በዓል አክብሩ አላለም። የግሪክ አማልክት ኢዎን (Aeon) በሚዘከርበት ቀን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የመፅሃፍ ቅዱስ እውቀት የሌለው ሰው ቢጠመቅ ትርጉሙ ምንድን ነው?

በዓላትን በተመለከተ ብዙ ጥቅስ ማስቀመጥ ይቻላል ፣ የፅሁፉ አላማ የጥምቀት በዓለ መፅሃፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ እንደሌለው ታሪካዊ መረጃ ማቅረብ ላይ ያተኮረ ነው።

http://aglobalworld.com/holidays-around-the-world/coptic-epiphany/

በኮከብ እየተመሩ የመጡት ሰባሰገል የእስራኤል አምላክን የሚያመልኩ አልነበሩም። ምክኒያቱም ኮከቡ በመጀመሪያ የወሰዳቸው ወደ ሄሮድ ነበር። ሄሮድም ህጻኑን ኢየሱስ ለማስገደል ባደረገው ሙከራ አእላፍት ህጻናት የግፍ ሰለባ ሆነዋል። የግሪክ ግኖስቲክ ኢየሱስ ከኢዮን አንዱ ነው ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ ሰባሰገልም በብርሃን ተመርተው ለልደቱ ገጽ በረከት ካመጡ፣ እንዲሁም የጥምቀቱንም ቀም በዓለ ብርሃናት በለው ከሰየሙት፣ በእርግጥ ይህ ቀን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ ያለው ክርስቲያናዊ በዓል ነውን?

ህዝበ-ክርስትናና የታቦት አምልኮ ሥርዓት

ክርስትናና ታቦት ምን አገናኛቸው? የሚል ጥያቄ አንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ታሪካዊ እውቀት ያለው ሰው አእምሮ ውስጥ የሚመላለስ መሪ ሃሳብ ነው። የአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን (ዓም) ክርስቲያኖች ይህንን የአምልኮ ሥርዓት አካሂደው ነበርን?

ዓለማዊ ታሪክም ይሁን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያረጋግጠው ኢየሱስ ምድር ላይ በነበረበት ዘመን የታቦት ሥርዓት ነበር? በፍጹም አልነበረም! መሲሁ (ኢየሱስ) ከመገለጡ ከአራት መቶ ዓመታት በፊት የእስራዔል የቃል ኪዳኑ ታቦት ዳግመኛ እንደማይሰራ በኤርምያስ ላይ ተገልጿል።— ኤር.3:16, 17

በግዞት ለሰባት አስርተ ዓመታት ቆይታ ያደረጉት እስራኤላውያንም ቢሆን (በ537 ዓ.ዓ) ከስደት መልስ በቀድሞው ቦታ አዲስ ቤተ መቅደስ ገንብተው ንጹህ አምልኮ ሲዋቀር የታቦት ሥርዓት አልነበረም።

በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዓ.ም (እዘአ) የነበሩ ክርስቲያኖች የአምላክን የምሥራች ዜና ከመስበክና ከማስተማር ውጭ የታቦትን የአምልኮ ሥርዓት አልተከተሉም።ከጌታ ኢየሱስ የተሰጣቸውም መመሪያ ይህ ነው፡- — ዮሐንስ 28፡ 19፣20

ቀድሞው የእስራኤል የቃል ኪዳን ታቦትና በህዝበ ክርስትና ታቦት ተብዬው መካከል ስላለው ልዩነት ምን ማለት ይቻላል? የእሥራኤል የቃል ኪዳን ታቦት ከህዝበ ክርስትና ታቦት ፈጽሞ የተለየ ነው።

የቃል ኪዳኑ ታቦት የተሰራው በእሥራኤል አምላክ በያህዌህ ትዕዛዝ ነው። ይህ ታቦት የተለያየ መጠሪያ አለው። የአምላክ ማደሪያ፣ግዚያው ማረፊያ፣የማደሪያው ድንኳን ..ወ.ዘ.ተ... ተብሎ ብመጠራት ይታወቃል። አምላክ የእሥራኤልን ጉባዔ

የራሱ ንብረት ሲያደርግ በመካከላቸው እንደሚገኝ የገባላቸው ቃል ኪዳን ነው ፣ የአምልኮ ስርዓትና ክንዋኔው ደንቡና ህጉ ከሃምሳ ባላነሱ ምዕራፋት ላይ ተገልጿል ዘጸአት 25:1-22 በማንበብ መረዳት ይቻላል።

አምላክ ለሙሴ ትዕዛዙን ከሰጠው በኋላ ዓመት ባልሞላ ጊዜ በ1512 ዓ.ዓ የድንኳኑን ሥራ አጠናቋል ፣ የእስራኤልም ጉባዔም የቃል ኪዳኑ ታቦት በመካከላቸው ስላለ አምላካቸው ያህዌን በመታዘዝ በረከትን አግኝተዋል ፣ ባለመታዘዛቸው ደግሞ መከራን ተቀብለዋል።

የቃል ኪዳኑ ታቦት ከ1512 ዓ.ዓ እስከ 1027 ዓ.ዓ ድረስ በድንኳን ውስጥ ቆይቷል ከዚያም ሰለሞን ባሰራው ቤተ መቅደስ ውስጥ ከ1027 ዓ.ዓ ጀምሮ ለመጨረሻ ግዜ እስከታየበት እስከ 642 ዓ.ዓ ድረስ ቆይቷል። – 2ኛ መዋዕለ ዜና 35:3

እሥራኤላውያን በባዕድ አምልኮ ቤተመቅደሱንና እራሳቸውን ስላረከሱ አምላክ አቋም ለመውሰድ ተገደደ ኤርምያስን ቃል አቀባዩ እንዲሆን ነቢይ አድርጎ አስነሳው(ኤርምያስ 1:18,19) ። ኤርምያስም በነቢይነት ከ647 ዓ.ዓ እስከ 580 ዓ.ዓ ያለውን ታሪክ ዘግቧል።

የቃል ኪዳኑ ታቦት ለመጨረሻ ጊዜ የታዬው ንጉስ ኢዮስያስ በነገሰ በ18ኛው ዓመት ኒሳን 14 642 ዓ.ዓ ነው (2 ዜና 35:19) ንጉስ ኢዮስያስም ታቦቱን በተመለከተ ለካህናቱ ልዩ ትዕዛዝ ሰጠ "ከዚህ በኋላ ታቦቱን በትከሻችሁ መሸከም አያስፈልጋችሁም" – 2 ዜና 35:3

ታዲያ የቃል ኪዳኑ ታቦት የት ገባ?

በወቅቱ የእስራዔል አምላክ የሾመው ነቢይ ነበር ፣ እሱ በወቅቱ የሆነውን ተመልክቷል ምስክርም ቃል አቀባይም ነበር። ኤርምያስ 3:16.17እንዲህ ይላል ፡- "ከእንግዲህ የይሖዋ የቃል ኪዳን ታቦት አይሉም፤ስለ እሱ አያስቡም፤ጨርሶ

አያስታውሱትም፣ወይም እንደጎደላቸው ሆኖ አይሰማቸውም፣ታቦቱም ዳግመኛ አይሰራም። "ኤርምያስ ስለ ታቦቱ የሚያውቀው ነገር አለን? ባያውቅ ኖሮ ይህንን ፍንጭ ባልሰጠ ነበር። ይህም የሆነው ኢየሩሳሌም በባቢሎናውያን ከመደምሰሷ ከሰላሳ ዓመት ቀደም ብሎ ነበር።

የቃል ኪዳኑ ታቦት በባቢሎናውያን ተወስዷልን? በፍጹም አልተወሰደም!

ኢየሩሳሌም በ607 ዓ.ዓ በባቢሎናውያን ስትደመሰስ የቤተ መቅደሱ የአምልኮ መገልገያ እቃዎች መወሰዳቸውን በዝርዝር ሲገለጹ ከሁሉም የሚበልጠው የቃል ኪዳኑ ታቦት ግን አልተገለጸም። (2 ነገሥት 25:13-17 ዕዝራ 1:7-11) እሥራዔላውያን ከሰባ ዓመቱ ግዞት በ537 ዓ.ዓ ከተመለሱ በኋላ ቤተ መቅደሱም በዘሩባቤል የበላይ አመራር ታድሶ የአምልኮ ሥርዓት ሲጀመር በቅዱስ ቅዱሳን ውስጥ የቃል ኪዳኑ ታቦት አልነበረም፣ ካህናቱም የአምልኮ ሥርዓታቸውን አላቆሙም።

የቃል ኪዳኑ ታቦት በአህዛብ ተወስዷል በለህ ታስባለህን?

ይህ የቃል ኪዳን ታቦት ባቢሎን፣ሮም ወይም ኢትዮጲያ ሄዷል በሎ ማሰቡ ስህተት መሆኑንና ፍጹም ለጣኦት አምላኪ አህዛብ ተላልፎ ሊሰጥ እንደማይችል መለኮታዊ የማስጠንቀቂያ ደወል ለመሆኑ በፍልስጤማውያን ላይ የደረሰው ለሌሎች ተሞክሮ እንዲሆን ነበር። — 1 ሳሙዔል 5:1-6, 12

ክርስቲያን ታቦትም ሆነ ጽላት ቀርጾ ማምለክ መጽሃፍ ቅዱሳዊ ነው?

ምንም አይነት ድጋፍ የለውም። በመጀመሪያ ደረጃ ታቦቱ በእስራኤል ጉባኤና በአምላካቸው ያህዌ መካከል የተደረገ የቃል ኪዳን ታቦት እንጅ ከአህዛብ ጋር የተደረገ ኪዳን አልነበረም። ወደ ዋናው ርእሰ ጉዳይ ስንመለስ የህዝበ ክርስትና ታቦት ተብየው ምን ይመስላል?

የግብጽ ኮፕት ኦርቶዶክስ ታቦቱን “ሉህ” ይሉታል ፅላት ወይም ሰሌዳ ማለት ነው። በእንግሊዘኛ (ታብሌት) እንደማለት ነው። ለአገላለጽ ያመች ዘንድ ሉህ (ሉኽ) በወረቀትም ሆነ ከእንጨት በተቀረጸ ጣውላ ሊገለጽ ይችላል። ይህ ማለት ገጽ ማለት ነው። በሰሌዳ ላይ የተጻፈ መልእክት ወይም ማስታወሻ ነው። ሆኖም ኦርቶዶክስ በሚል እንጅ ከኢትዮጲያው ፅላት ልዩነት አለው።በዚህ ጽላት ላይ አስርቱ ትዕዛዛት እንዲሁም የጣኦት አምልኮ መገለጫ የመስቀል ምልክትና የመሳሰሉት ነገሮች ተካተውበታል። ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት የሌላቸውን ሰዎች በጣኦት አምልኮ ተተብትበው በመንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ እንዲጓዙ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።ይህንን ባለ አራት ማእዘን ጣውላ

በቀይ ጨርቅ በመጠቅለል በቀሳውስት አናት ላይ በመጫን ህዝበ ክርስትና በየአመቱ በህይወት የሌሉ ቅዱሳንን ትዘክራለች የሙታን መናፍስትን በማሰብ የአምልኮ ሥርዓት ታካሂዳለች። በእርግጥ ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነውን? መልሱን ላንባቢያን ይሁን።

ይህ 40x40 ሴ.ሜ የሆነ ምስል እንዴትና ከምን እንደሚቀረጽ ይህን ሊንክ በመጫን ማንበብ ይቻላል።

https://en.wikipedia.org/wiki/Tabot

ኢየሱስም ሆነ ሃዋርያቱ በአጠቃላይ የመጀመሪያው ዘመን ክርስቲያኖች የታቦት አምልኮ ስርዓትን አላደረጉም! ለምን ዕብራውያን 7:18 እንዲህ ይላል ፦" ህጉ የትኛውንም ነገር ወደ ፍፅምና አላደረሰውምና ወደ አምላክ የምንቀርብበት የተሻለ ተስፋ መስጠቱ ግን ይህንን ማድረግ ችሏል።"

ምድራዊ የቃል ኪዳኑ ታቦት የማያስፈልግበትን ምክንያት ሲገልፅ ደግሞ ፣ ክርስቶስ በሰው እጅ ወደላተሰራችው ፍፁም ወደ ሆነው ድንኳን የገባው የኮርማና የወይፈን ደም ይዞ ሳይሆን የገዛ ራሱን ደም ይዞ ወደ ሰማያዊ ድንኳን ገብቶ ሊቀ ካህን እንደሆነ ይገልጻል። — ዕብራውያን 9:1-28 እንዲሁም 8:1-13 ሙሉ በሙሉ አንብቦ ለመረዳት ይቻላል።

ለማሳረጊያ ያህል ህጉ ወደፊት ለሚመጡት ነገሮች ጥላ ነው ሲል ዕብራውያን 10:1ሲል ይደመድማል! በመጨረሻም ዮሃንስ በምሳሌያዊ አገላለጽ የቃል ኪዳኑን ታቦት በሰማይ እንዳየው በራዕይ 11:15,18 ላይ ይገልፃል።

እንደ ውስጣዊ ዘገባ ኢትዮጲያ ውስጥና ውጭ ቁጥራቸው አስር ሽህ የሚሆኑ ፅላት (ታቦት) እንዳሉ ይነገራል። ፅላቶቹ የተሰየሙት አንዳንዶቹ በመላዕክት ፣ በሚታወቁና በማይታወቁ ቅዱሳን እንዲሁም ፖለቲከኞችና ጦረኞች ስም ነው። በዘመናችን ህዝበ ክርስትና ለብዙ ተከፋፍላለች። የተዋህዶ እናት የሆነው የኮፕት ኦርቶዶክስ ልዩነት አለው። የምስራቅም ሆነ የምእራብ የህዝበ ክርስትና ተቋማት በእምነትም ሆነ በቀኖና አንዳቸውም ካንዳቸው አይገናኙም። መጽሐፍ ቅዱስ ግን አንድ ነው። ታዲያ እነዚህ ክርስትናን እንወክላለን የሚሉ ብሄራት የታቦት አምልኮ ሥርዓት ያካሂዳሉ?

የእስራኤል የቃል ኪዳን ታቦት በንግስተ ሳባ ዘመን ወደ ኢትዮጲያ ግብቷል ለሚባለው ይተወሰኑ ታሪካዊ መረጃ ጣል ማድረጉ ተገቢ ነው። በንግስተ ሳባ ዘመን የእስራኤል ታቦት ወደ አክሱም መምጣት አፈ-ታሪክ ነው

1ኛ. ንግስተ ሳባ ሰለሞንን የጎበኘችው በአሥረኛው መቶ ዓ.ዓ ነው፣ በዚያን ግዜ የአክሱም ዘመነ መንግስት በህይወት አልነበረም የአክሱም መንግስት ማቆጥቆጥ የጀመረው በሶስተኛው መቶ ዓ.ም (እዘአ) ነው።

http://www.newworldencyclopedia.org/entry/Axum
http://www.onislam.net/english/culture-and-entertainment/history/413807-axum-the-ancient-civilization-of-ethiopia.html
https://en.wikipedia.org/wiki/Kingdom_of_Aksum

2ኛ. ንግስተ ሳባ የሄደችው ከደቡብ አረቢያ ነው ስሟም ቢልቂስ ይባላል። ታሪኩን በዊኪፒዲያም ሆነ በሌሎች ድረገጽ ፈልጎ ማግኘት ይቻላል።

http://womenshistory.about.com/od/bible/a/Queen-Of-Sheba.htm
http://www.bbc.co.uk/history/ancient/cultures/sheba_01.shtml
http://www.ucalgary.ca/uofc/events/unicomm/NewsReleases/queen.htm

3ኛ. የቃልኪዳኑ ታቦት በአሥረኛው መቶ ዓ.ዓ (ዘአበ) ከሳባ ጋር መጥቷል ከተባለ ፣በስድስተኛው መቶ ዓ.ዓ (642 ዘአበ 2ኛ ዜና 35:3) ታቦቱ በኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ውስጥ እንደነበረ መጽሃፍ ቅዱሳዊም ታሪካዊም መረጃ አለ።

http://www.allaboutarchaeology.org/when-did-the-ark-of-the-covenant-disappear-faq.htm
https://en.wikipedia.org/wiki/Tabot
https://en.wikipedia.org/wiki/Tabuik

ክርስቲያን ታቦት ቀርጾ እንዲያመልክ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ አለው?

ክርስቶስ በሰው እጅ ወደላተሰራችው ፍፁም ወደ ሆነው ድንኳን የገባው የኮርማና የወይፈን ደም ይዞ ሳይሆን የገዛ ራሱን ደም ይዞ ወደ ሰማያዊ ድንኳን ገብቶ ሊቀ ካህን ሆኖል። — እብራውያን 9:1-28

ከወር መጀመሪያ እስከ ወር መባቻ የሚዘከሩ በዓላት

እነዚህ በዓላት ክርስቲያናዊ ናቸውን?

1ኛ. ልደታ ማርያም 2ኛ. አባጉቦ ታዲዮስ 3. ባታ 4. ዮሐንስ ሃዋርያው 5. አቦ 6. ኢየሱስ 7. ስላሴ 8. አባ ኪሮስ 9. ጨርቆስ 10. መስቀለ ኢየሱስ 11. ሃና ማርያም 12. ሚካኤል 13. እግዜብሄር አብ 14. አቡነ አረጋዊ 15. ቂርቆስ 16. ኪዳነምህረት 17. እስጢፋኖስ 18. ቶማስ 19. ገብርኤል 20. ህንጻተቤለማርያም 21.ማርያም 22. ኡራኤል 23. ጊዮርጊስ 24. ተክለሃይማኖት 25. መርቆርዮስ 26.ዮሴፍ 27. መድህንያለም 28. አማንኡኤል 29. በአለእግዜአብሄር 30. ዮሀንስ/ማርቆስ

ከወር መጀመሪያ እስከ ወር መባቻ ድረስ በክርስትና ሥም የሚከበሩ በዓላት መጽሐፍ ቅዱሳን መሰረት ያደረጉ አይደሉም ። ነገር ግን የታሪክ ድርሳናት በዓላቱን በተመለከተ አመጣጡን ሲዘግብ ፡- የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሙታንን መናፍስት ለማስታወስ ይህንን የነፍሳት ሁሉ ቀን (All Souls Day) እንዲሁም ወደ ሰማይ የሄዱትን ሰዎች ቅዱሳንን ለመዘከር በሚል ከአስራ ሶስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንዲከበር ደነገጉ። ይሁን እንጅ የዚህ በዓል አከባበር ከክርስትና በፊት ከነበሩ አረማውያን ልማዶች ጋር የተቆራኘ ነው። ይኸውም የሴልቲክስ ካህናት የአስማትና የጥንቆላ ሥርዓት አከባበር የመጡ ናቸው። በማለት ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ በቂ ጽሁፋዊ መረጃ ያቀርባል።

http://www.britannica.com/EBcheck.../topic/15924/All-Souls-Day

ይህ ለምን ሊሆን ቻለ?

ሁለተኛ መቃቢስ 15:11-16 የተጠቀሰው “የሙታንን ስለ ሕያዋን ምልጃ” ለመደገፍ በሚደረገው ጥረት ነው። ብዙ ምሑራን እንደሚሉት 2 መቃብያን የተጻፈው በአምላክ መንፈስ መሪነት አልነበረም። ከአዋልድ መጻሕፍት አንዱ ነው። በመንፈስ መሪነት የተጻፈውን የአምላክ ቃል የመጽሐፍ ቅዱስን ምሥክርነት ለመቀበል አትመርጥም? በእሱ ልትተማመንበት ትችላለህ፤ ምክንያቱም ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል:- “የእግዚአብሔር ሰው ፍፁም ብቁና ለበጎ ነገር ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ ናቸውና ለማስተማርም ለተግሣጽ፣ ለማቅናት እና በቅድስናም ለማስተማር ይጠቅማሉ። ሥራ።”—2 ጢሞ. 3:16, 17፣

https://www.google.ca/url…
https://openlibrary.org/…/OL6952150M/The_worship_of_the_dead
https://www.google.ca/url?sa=t&rct=j&q=&esrc=s&source=web&cd=3&cad=rja&uact=8&ved=0CCgQFjAC&url=http%3A%2F%2Fwww.catholic.org%2Fsaints%2Fallsouls%2F&ei=jUWhVbDvAcqANrPchMgH&usg=AFQjCNFDBLPYECzSo5lDrJhKUxH7qbFe8A

የሮማ ካቶሊክ የሌሎች ህዝበ ክርስትና እናት በመሆንዋ፣ቀደም ብሎ በሶስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኒቂያ ባደረጉት ኢ-ክርስቲያናዊ ድንጋጌ የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የቅዱሳንና የሙታን መንፈስ የመዘከር ጉዳይ ተቀብለዋል። በፍትሃ- ነገስት አንቀፅ 20 ገፅ 191 ቁጥር 768 ሰማዕት በዓላቸው ይከበር ይላል። እንዲሁም አንቀፅ 22 መታሰቢያ እንዲደረግላቸውና መስዋዕት እንዲሰዋላቸው ይላል።

https://www.google.ca/url?sa=t&rct=j&q=&esrc=s&source=web&cd=4&cad=rja&uact=8&ved=0CC4QFjAD&url=http%3A%2F%2Fcatholicism.about.com%2Fod%2Fholydaysandholidays%2Fp%2FAll_Souls_Day.htm&ei=jUWhVbDvAcqANrPchMgH&usg=AFQjCNEignyycz6hrBlpGmwZlu2xZJAOpw

ፍትሃ-ነገስትም የሙታን መታሰቢያ እንዲደረግ የሚለውን የካቶሊክ ድንጋጌ ተግባራዊ አድርጓል። በየሃገራት የሚገኙ የህዝበ ክርስትና ድርጅቶች ገድል ሰሩ ለተባሉ ቅዱሳን ሰዎች ብሄራዊ የመታሰቢያ ቀን ይሁንላቸው ይላል። አንቀጽ 20

የቡሄ (መላጣ ገላጣ) በዓል

በእርግጥ ምንጩ ክርስቲያናዊ ነውን?

አይደለም! ይህንን በዓል ክርስቲያን እንዲያከብረው ምንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ ባይኖረውም፡የዚህ በዓል ስረዓተ ምንጭ የሆነችው የኮፕት ኦርቶዶክስ ህዝበ ክርስትና ኢየሱስ በታቦር ተራራ ላይ በተዓምራዊ ሁኔታ መልኩ ተለውጦ በክብሩ የታየበት ቀን ስልሆነ ይህንን ቀን እናከብረዋለን ትላለች ። (ማቴዎስ 17:1-3, 16:28) በተመሳሳይ ይህንን በዓል ከኮፕት የተቀበለችው ተዋህዶም ተመሳሳይ መልስ ትሰጣለች።

የተዋህዶ ኦርቶዶክስ ስለ ቡሄ ስትገልጽ፡- ቡሄ ማለት “መላጣ ገላጣ” ማለት ነው። አክሎም “የክረምቱ አፈና ተወግዶ የብርሃን ወገግታ የሚታየው በዚሁ በዓል አካባቢ ስለሆነ ቡሄ ያሉት ለዚህ ሳይሆን አይቀርም።” ትላለች ግራ በተጋባ ሁኔታ! ለተዋህዶ የዚህ በዓል ታሪካዊ አመጣጥ ህልምና ቅዠት የተቀላቀለበት ክስተት ነው።

http://books.good-amharic-books.com/eochist-2.pdf ገጽ 41

ሆኖም ይህ በዓል በተዋህዶ ህዝበ ክርስትና በአራተኛ ደረጃ የሚከበር ነው። ኢየሱስ መልኩ የተለወጠበት ቀን ከሆነ በዳቦና በችቦ ቀኑን ለማክበር ለምን አስፈለገ? ይህ ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተገልጿልን?

በመጀመሪያ ደረጃ ኢየሱስ መልኩ የተለወጠበትን ቀን ክርስቲያን እንዲያከብረው አላዘዘም። ይህ በኢትዮጲያ ነሐሴ 13 ወይም በኮፕት አቆጣጠር መስራ 13 (Masra) በዳቦና ቹቦ በማብራት እንዲሁም በሆያ ሆዬ የሚደምቀው ይህ በዓል ከክርስትና በፊት በዚህ ወር ይከበር እንደነበር በቂ ታሪካዊ መረጃ አለ።

መስ-ራ (Mas-ra) የተባለው ወር ራ-ra የተባለው የፀሐይ አምላክ የተወለደበት ወር ነው። ይህ የጸሐይ አምላክ የአማልክት ሁሉ አባት እንደሆነ ድረ-ገጹ ያትታል።

http://www.egyptartsite.com/ra.html
https://en.wikipedia.org/wiki/Coptic_calendar

ከክርስትና በፊት በግብጽ ይከበር ስለነበረው የአረማውያን የጣኦት ስርዓት አምልኮ ዳቦ በመብላትና ችቦ በማብራት ራ-ra የተባለው አማልክት ይዘከር እንደነበር ታሪክ ይዘግባል። (Egyptian god ra rituals and bread sacrifice) "የግብጽ አምላክ ሬ-ra አምልኮና የዳቦ መስዋእት።"

https://books.google.ca/books?id=5uQdDAAAQBAJ&pg=PA129&lpg=PA129&dq=egyptian+god+ra+rituals+and+bread+sacrifice&source=bl&ots=dqGc5G_gh3&sig=02QuimRW_x_mQ7XWYOfRgjgSCFc&hl=en&sa=X&ved=0ahUKEwj8ja71zKXOAhUJ64MKHT15BZwQ6AEISTAI#v=onepage&q=egyptian%20god%20ra%20rituals%20and%20bread%20sacrifice&f=false

የኮፕት ህዝበ ክርስትናም የተባረከ መስራ (the blessed mas-ra) ስትል በደስታ ትገልጸዋለች። ተዋህዶም በቀሳውስት ቡራኬ ዳቦ በመብላትና ችቦ በማብራት በሆታና በጭፈራ እንዲሁም በገጠሩ የሃገሪቱ ክፍል ጅራፍ በማጮህ (ሬ ቡሄ መላጣ ገላጣ የጸሐይ አምላክ) በክርስትና ሥም ተዘክሮ ይውላል።

http://st-takla.org/Full-Free-Coptic-Books/Coptic-Synaxarium-or-Synaxarion_English/12-Mesraa/Coptic-Calendar_13-Mesra.html

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያስተምራል?

- "ታማኝ ያልነበሩት እስራኤላውያን] ከሕዝቦቹ ጋር ተደባለቁ፤ ልማዳቸውንም ቀሠሙ።" — መዝሙር 106:35

- "በትንሽ ነገር ታማኝ የሆነ ሰው በብዙ ነገርም ታማኝ ነው፤ በትንሽ ነገር ዓመፀኛ የሆነ ሰው ደግሞ በብዙ ነገርም ዓመፀኛ ነው።"—ሉቃስ 16:10

- “የዓለም ክፍል [አይደላችሁም።]”—ዮሐንስ 15:19
- “‘ከያህዌ ማዕድ’ እና ከአጋንንት ማዕድ መካፈል አትችሉም።”—1 ቆሮንቶስ 10:21

- የጣዖት አምልኮ በመካፈል የአሕዛብን ፈቃድ እየፈጸማችሁ ትመላለሱበት የነበረው ያለፈው ጊዜ በቂ ነው።”—1 ጴጥሮስ 4:3

- የአምላክን ቅዱስ መንፈስ የሚቃረነው ‘የዓለም መንፈስ’ የሚንጸባረቅበት ነው?—1 ቆሮንቶስ 2:12፤ ኤፌሶን 2:2

- በሥነ ሥርዓቱ ላይ ብካፈል ሌሎች ይሰናከላሉ?—ሮም 14:21

- በሥነ ሥርዓቱ ላይ ላለመካፈል ከወሰንኩ ምክንያቴን ለሌሎች አክብሮት በተሞላበት ሁኔታ ማስረዳት የምችለው እንዴት ነው?—ሮም 12:1, 2፤ ቆላስይስ 4:6

የፋሲካ ትንሳኤ በዓል (ኢስተር፣ኢሽታር)

በዓለ ትንሣኤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ የለውም።ኢየሱስ እንዲዘከርለት ያዘዘው የሞቱን መታሰቢያ እንጂ ትንሣኤውን አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በተገለጸው የጨረቃ አቆጣጠር መሠረት የሞቱን መታሰቢያ በየዓመቱ መከበር ይገበዋል።— ሉቃስ 22:19, 20

ክርስቲያናዊ ካልሆነ ታሪካዊ አመጠጣ ከየት ነው?

የስምንተኛው መቶ ዘመን የካቶሊክ ምሁር ቨኔራብል ቤዴ ቃሉ ከአንግሎ ሳክሰን የፀደይ አምላክ "ኢኦስትሬ" ስም የተገኘ ነው ሲሉ ተናግረዋል። አሌክሳንደር ሂሎፕ ዘ ቱ ባቢሎን በተባለው መጽሐፉቸው በፋሲካ እና በባቢሎናዊቷ አምላክ አስታርቴ መካከል ግንኙነት እንዳላቸው ተናግሯል። ወይም በግዕዝና በአማርኛው አጠራር "አስተረዮ" በመባል የምትታወቀው ናት።

የፋሲካ በዓል እንደ በዓል መደረጉ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ አልነበረም። እንዲያውም ምሑራን ፋሲካ የሚለው ቃል የአንግሎ ሳክሰን ምንጭ ነው ይላሉ፤ የፀደይ ወቅትን ያመለክታል። በዚያ ወቅት የጥንት ሰዎች ፀሐይ ከክረምት ሞት በኋላ እንደገና እንደምትወለድ ያስቡ ነበር፤ እንደ ፓኬስ ወይም ፓስኳ ያሉ ሌሎች የበዓላት አገላለጾች የተገኙት ከጥንታዊው የዕብራይስጥ ቃል ፔሳች ወይም "ፋሲካ" ነው። ሕዝበ ክርስትና ፋሲካ ይህን የአይሁድ በዓል እንደሚተካ ትናገራለች። ይህ ግን ኢየሱስ ፋሲካን የተካው በፋሲካ ሳይሆን በመታሰቢያ እራት የመሆኑን እውነታ ችላ ብሎታል።

https://www.history.com/topics/holidays/history-of-easter
https://www.britannica.com/topic/Easter-holiday

ስለዚህ የጥንቱ የጸሐይ አምልኮ የክርስትና ካባ ለብሶ ክርስቲያናዊ ይዘት እንዲይዝ መደረጉ በምንም መልኩ የክርስቲያን በዓል ሊያስብለው አይችልም።

ይህንን በተመለከተ በኒቂያ መማክርት ተደንግጎ በኮፕት ኦርቶዶክስ መሻሻያ ተደርጎለት በ14ኛው ዓ.ም የተዋህዶ ስርዓተ መተዳዳሪያ የሆነው ፍትህ ነገስት **አንቀጽ 14 ገጽ 184 በቁጥር 731** እንደተገለጸው:- የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳዔ ከዕለተ እሁድ ብቻ በስተቀር አታድርጉ ፣ ዶሮ በጮኸም ግዜ ብሉ። **ቁጥር 733** ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተንስቷልና ይኸውም የትንሣኤያችን አረቦን ነው። **ድስቅ 30 ቁጥር 729 ገጽ 183** በክቡር ደሙ የዋጀችሁ ስለሆነ በዓለ ፋሲካን ታከብሩ ዘንድ ይገባችኋል። ይላል!

በአውሮፓ የካቶሊክ ህዝበ ክርስትና ታሪካዊ አመጣጡን በይፋ በሰነድ ካስቀመጠ ከስድስት መቶ ዓመታት በኋዋላ በኢትዮጲያ እንዲከበር ተዋህዶ ድንጋጌውን በጭፍን ተቀብላለች። እውነታው ግን የትንሳኤ ፀሐይ መውጣት በየአመቱ ጣኦት አምላኪ ከሆኑት አረማውያን ዝክረ አስታሬት የመነጨ ነው።

የገና በዓል (ልደት)

ልክ እንደ ሌሎቹ በዓላት ይህ ቀን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ ያለው ክርስቲያናዊ በዓል ነው? ታሪክም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያረጋግጡት አይደለም!

በታሪክ እንደተቀመጠው የገና በዓል (ልደት) መከበር የተጀመረው በ336 ዓ.ም በንጉስ ኮንስታንቲን ስርወ-መንግስት ነው። ከጥቂት ዓመታት በኋላ በ353 ዓ.ም የሮማው ጳጳስ ጁሊይስ ቀዳማዊ ዲሰምበር 25 የኢየሱስ ልደት ተብሎ እንዲከበር ወሰነ። ይህ ማለት ለሶስት መቶ ዓመታት ያህል ይህ በዓል አይከበርም ነበር። የመጀመሪያው ዘመን ክርስቲያኖቹም አላከበሩትም።

http://www.whychristmas.com/customs/25th.shtml
http://www.sermoncentral.com/illustrations/sermon-illustration-stories-christmas-22732.asp
https://en.wikipedia.org/wiki/Pope_Julius_I

ታዲያ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ የሌለው ልደት ለምን በዚህ ቀን እንዲከበር ተፈለገ ልሚለው ደግሞ ኢየሱስ በታኅሣሥ 29 (ወይም እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ታኅሣሥ 25) መወለዱን የሚያሳይ መረጃ ከሌለ ገና በዚህ ወቅት የሚከበረው ለምንድን ነው? ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ እንደሚናገረው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቅዝቃዜው ወቅት መገባደጃ ላይ ያለውን ይህን ቀን የመረጡት "'ድል የማትደረገው ፀሐይ የልደት ቀን' ከሚከበርበት የሮማውያን አረማዊ ክብረ በዓል ጋር እንዲገጣጠም ፈልገው" ስለነበረ ይመስላል። ኢንሳይክሎፒዲያ አሜሪካና እንደሚናገረው ከሆነ ይህ የተደረገው "ከአሕዛብ ለመጡ ሰዎች ክርስትና ይበልጥ ማራኪ እንዲሆን ታስቦ" እንደሆነ አብዛኞቹ ምሁራን ያምናሉ።

https://www.britannica.com/topic/Christmas
http://rayharvey.org/index.php/tag/the-encyclopedia-americana/

ቀጥሎ የቀረቡት የማመሳከሪያ ሥራዎች እንደሚያሳዩት መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበትን ቀን አይናገርም፡-

ክርስቶስ የተወለደበት ትክክለኛ ቀን አይታወቅም።

https://www.britannica.com/topic/Christmas
https://www.newworldencyclopedia.org/entry/Christmas
https://www.britannica.com/topic/Saturnalia-Roman-festival
http://www.biblicallifestyleseminars.org/Christmas.html

መጽሐፍ ቅዱስ ‘ኢየሱስ የተወለደው መቼ ነው?’ ለሚለው ጥያቄ ቀጥተኛ መልስ ባይሰጥም ብዙዎች ኢየሱስ የተወለደው በታኅሣሥ 29 (ወይም እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ታኅሣሥ 25) እንዳልሆነ እንዲያምኑ ያደረጓቸውን በኢየሱስ ልደት ወቅት የነበሩ ሁለት ነገሮችን ይጠቅሳል።

- የሕዝብ ቆጠራ። ኢየሱስ ከመወለዱ ትንሽ ቀደም ብሎ አውግስጦስ ቄሳር “የዓለም ሕዝብ ሁሉ እንዲመዘገብ አዋጅ አወጣ።” እያንዳንዱ ሰው “ወደየራሱ ከተማ” በመሄድ መመዝገብ ይጠበቅበት ነበር፤ ይህም ለአንድ ሳምንት ወይም ከዚያ በላይ ጉዞ ማድረግን ይጠይቅ ይሆናል። (ሉቃስ 2:1-3) ይህ ትእዛዝ የወጣው ግብር ለመሰብሰብ ወይም ወታደሮችን ለመመልመል ታስቦ ሊሆን ይችላል፤ አዋጁ የወጣው መቼም ይሁን መቼ፣ አብዛኛው ሕዝብ እንዲህ ያለ ጉዞ ማድረግ እንደማይፈልግ ግልጽ ነው። በመሆኑም አውግስጦስ በቅዝቃዜው ወቅት እንዲህ ያለ ጉዞ እንዲያደርጉ የሚያስገድድ አዋጅ በማውጣት አብዛኛውን ሕዝብ የሚያስቆጣ ድርጊት እንደማይፈጽም የታወቀ ነው።

- በጎች። በዚያን ወቅት “ሌሊት ሜዳ ላይ መንጎቻቸውን ሲጠብቁ የሚያድሩ እረኞች ነበሩ።” (ሉቃስ 2:8) ዴይሊ ላይፍ ኢን ዘ ታይም ኦቭ ጂሰስ የተባለው መጽሐፍ “ከፋሲካ በዓል [የመጋቢት አጋማሽ] በፊት ካለው ሳምንት አንስቶ እስከ ኅዳር አጋማሽ ድረስ” መንጋዎች ሜዳ ላይ ያድሩ እንደነበር ተናግሯል። አክሎም እንዲህ ብሏል:- “መንጋዎቹ ክረምቱን የሚያሳልፉት በጉሮኗቸው ውስጥ ሆነው ነበር። እረኞች መንጋቸውን ሲጠብቁ በሜዳ ማደራቸውን ከሚናገረው የወንጌል ዘገባ አንጻር ሲታይ የገና በዓል ቅዝቃዜ በሚበረታባቸው ወራት መከበሩ ራሱ ቀኑ ፈጽሞ ትክክል እንዳልሆነ ያስገነዝባል።”

ሆኖም ኢየሱስ ከሞተበት ከኒሳን 14 ቀን 33 ዓ.ም. የጸደይ ወቅት ተነስተን ወደ ኋላ በመቁጠር የተወለደበትን ወቅት መገመት እንችላለን። (ዮሐንስ 19:14-16) ኢየሱስ ሦስት ዓመት ተኩል የፈጀውን አገልግሎቱን ሲጀምር 30 ዓመቱ ገደማ ነበር፤ ስለዚህ የተወለደው በ2 ዓ.ዓ. በነበረው የመጸው መግቢያ ላይ ነበር ማለት ይቻላል።—ሉቃስ 3:23

ሌላው ደግሞ የገና ዛፍ ጉዳይ ነው። "የዛፍ አምልኮ አረማውያን በሆኑ አውሮፓውያን ዘንድ የተለመደ ሲሆን ወደ ክርስትና ከተለወጡ በኋላም ቀጥሏል።" "በቀዝቃዛዎቹ ወራት አጋማሽ ላይ . . . የገና ዛፍን በበር ላይ ወይም በቤት ውስጥ የማስቀመጥ ልማድ በክርስትና ስም የዛፍ አምልኮ መቀጠሉን ያመለክታል።

በሌላ በኩል "የጥንቶቹ ክርስቲያኖች የማንኛውንም ሰው የልደት በዓል ማክበርን አረማዊ ልማድ አድርገው ይመለከቱት ስለነበር [የኢየሱስን] ልደት አላከበሩም።"

http://www.cogwriter.com/birthdays.htm

ስለዚህ ኢየሱስ የተወለደው በቅዜቃዜ ወቅት አይደለም። ይሁን እንጅ ስለ ገና በዓል የተዋህዶ ኦርቶዶክስ ምን ትላላች? የገናን በዓል በተመለከተ ለኢትዮጲያ ቤተክርስቲያን ራስ የነበረው የኮፕት ኦርቶዶክስ በፍትሃ-ነገስት አንቀጽ 19 ቁጥር 725 ገጽ 183 ላይ በግብጻውያኑ አቆጣጠር በታህሳስ 29 ቀን በየዓመቱ እንዲከበር በአዋጅ ደንግጓል።

መከበር የጀመረበት ትክክልኛው ግዜ ባይታወቅም፣ፍትሃ-ነገስት በስራ ላይ የዋለው በ14ኛው ክፍለ ዘመን በሃፀይ ዝረዓ-ያቆብ ስረወ መንግስት እንደሆነ ታሪኩ ያትታል። እንደዘገባው ይህ በዓለ በኢትዮጲያ መከበር የጀመረው ኢየሱስ ከተወለደ ከ1400 ዓመታት በኋላ መሆኑ ነው።

http://cdn.good-amharic-books.com/fiteha-9-cr.pdf

http://cdn.good-amharic-books.com/fiteha-1-cr.pdf

ስለዚህ ከላይ እንደተገለጸው ይህ ቀን የኢየሱስን ልደት ለመዘከር ሳይሆን ድል አድራጊዋን የጸሐይ ልደትን ለማክበር ስለሆነ ታሪካዊም ሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ የለውም።

የገና በዓል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ አለው?

ኢየሱስ የተወለደው በታኅሣሥ 29 ነው?